# ወቅታዊ የ COVID-19 ማጠናከሪያ ዙር ክትባት

ወቅታዊ የሆኑት የሞደርና እና የፋይዘር የማጠናከሪያ ዙር ክትባቶች፣ እንዲሁም **“bivalent” ክትባቶች ተብለው የሚጠሩት ክትባቶች የኦሚክሮን (Omicron) ተለዋዋጭ በሽታን** እና የመጀመሪያዎቹን የተለያዩ የ COVID-19 በሽታዎች ይከላከላሉ።





የማጠናከሪያ ዙር ክትባቶች ሌሎቹ የCOVID-19 ክትባቶች የሚጠቀሙትን ተመሳሳይ ንጥረ ነጋሮች ነውየተጠቀሙት፣ ነገር ግን አንዱ ፕሮቲን የኦሚክሮን (Omicron) ተለዋዋጭ በሽታን ለመከላከል ተቀይሯል።

**ከዚህ በታች የተጻፉት ነገሮች የሚመለከቶት ከሆነ የማጠናከሪያ ዙሩን ክትባት መውሰድ አለቦት:**

- የመጀመሪውን ተከታታይ ክትባት ጨርሰው ከሆነ፣ **እና**
- የመጨረሻውን ክትባት ወይም የማጠናከሪያ ዙሩን ክትባት ከወሰዱ ቢያንስ 2 ወራት አልፎት ከሆነ






የሞደርናን ወይም የፋይዘርን ወቅታዊ የማጠናከሪያ ዙር ክትባት ለመውሰድ መምረጥ ይችላሉ። የሚወስዱት ክትባት መጀመሪያ ከወሰዱት ተከታታይ ክትባት ወይም መጨረሻው ላይ ከወሰዱት የማጠናከሪያ ዙር ክትባት ጋር ተመሳሳይ መሆን የለበትም (ከ 5 አመት በታች ካልሆነ በስተቀር)።

የCOVID-19 ክትባት እና የማጠናከሪያ ዙር ክትባቶች ሁልጊዜም **ነጻ** ናቸው። የኢንሹራንስ ወይም የዜግነት ማረጋገጫ አያስፈልግም።





የወቅታዊ የማጠናከሪያ ዙር ክትባቶችን በሕዝብ ጤና አበርን (Auburn) የገበያ አዳራሽ የክትባት ክሊኒክ እና ከሌሎች የጤና እንክብካቤ አቅራቢዎች ፣ ክሊኒኮች እና ፋርማሲዎች ላይ ማግኘት ይችላሉ።

ለቋንቋ ትርጉም የዋሽንግተን ስቴት COVID-19 የመረጃ መስመር በ**1-800-525-0127**ይደውሉ እና **#ን ይጫኑ** (መስመሩን ሲያገኙ የመረጡትን ቋንቋ ይጠይቁ)። ለአካል ጉዳተኞች አቅርቦት፣ ኢሜል በ**publichealthaccommodations@kingcounty.gov** ላይ ያድርጉ

**ለበለጠ መረጃ፣ ወደ kingcounty.gov/vaccine/amharic ይሂዱ**